# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የተሰጠ አስቸኳይ ጥሪ
## የአሸባሪዎችን አገዛዝ ለመግታት በጋራ እንነሳ!

**ክፍል አንድ፤**

የኢትዮጵያ ሕዝብ በመስዋዕትነት የተጎናፀፋቸውን የግንቦት ሰባት ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ድሎች ተነጥቆ እነሱን መልሶ እጁ ለማስገባት ከጥቂት ፀረ-ሕዝብ የደምና የሥልጣን ጥመኞች ጋር የተያያዘው ትንንቅ አዲስ ምዕራፍ ውስጥ እየገባ ነው፡፡ በሰኔ ወር በአዲስ አበባ ከተማ የፈሰሰው የወጣት ዜጎቻችን ደምና የወላጅ እንባ ሳይደርቅ በአናት በአናቱ ግፍ፥ አፈናና ግድያ ሲፈጽሙ የቆዩ የኢሕአዴግ መሪዎች ይኸንን የሕዝባዊ ትግል ማዕበል ጨርሶ መቋቋም ባለመቻላቸው እነሆ ዛሬ ደግሞ በንጹኀን ደም የተጨማለቀው እጃቸው እንደገና በንጹህ ልጆቻችን ደም እየታጠበ ይገኛል፡፡

ዓለም-አቀፍ ኅብረተሰብ የተባለውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፋሽስታዊ መዓት እየዘነበበት "ሁለቱም ወገኖች" ከአመፅና ፀጥታን ከሚያውክ ማንኛውም ድርጊት እንዲቆጠቡ በሚል ከመቀጣጠብ ውጭ የወሰደው እርባና ያለው እርምጃ የለም፡፡ በነዚህ ጥቂት የሥልጣንና የደም ጥመኞች አማካይነት በመፈጸም ላይ ባለው መጠን የለሽ ግፍ ሳቢያ ተራ ሞት አምላክ ለሰው ልጅ እንደተለገሰው ፀጋ ሆኖ የሚናፈቅበት ወቅት ውስጥ ገብተናል፡፡ ሚስት ባሌን ቀጥቅጣችሁ ሳይሆን በጥይት ግደሉልኝ ብላ እስከመማጸን ስትደርስ፥ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ጎዳና ተዳዳሪ እርጉዝ ሴት ከአረመኔው ሥርዓት ጦር ስትሸሽ አስወርዷት እዛው የወደቀችበት ስትረሸን፥ የአምስት ልጆች እናት ልጇን ከጥይት ዝናብ ለማዳን በሞከረች እራሷ የጥይት እሩምታ እራት ሆና ልጆቿን በትና ስትሰዋ፥ አባቶች ልጆቻቸው ፊት፥ ልጆች አባት እናት እያዩ የጥይት እራት ሲሆኑ፥ ሚስት ባሌን አትውሰዱብኝ ብላ በተማፀነች ስትረሸን በእርግጥ አገራችን እንዲህ ዓይነቱ የምፅዓት ወቅት ውስጥ መግባቷን ያሳየናል፡፡ በመቶ ሺህ የሚገመቱ ልጆቻችን/ዜጎቻችን ከቤታቸው በጠራራም በውድቅት ሌሊትም እየታፈሱ ለወባ፥ ለኮሌራ፥ ለዱር አውሬ፥ ወዘተ... ተጋልጠው ወደሚያልቁባቸው አደገኛ አካባቢዎች ተወስደው እየታጎሩ ሊያመልጡ የሞከሩት የአዞና የሌሎች አራዊት እራት እየሆኑ፥ የቀሩት በረሃብ እየተሰቃዩ፥ ለአቅመ-ሔዋን ያልደረሱ ሴቶች ልጆቻችን ሳይቀሩ ለግድ ወሲብ እየተዳረጉ የሰው ሕይወትና ሰብአዊ ክብር ከምንም መቆጠሩ ባከተመበት ሁኔታ ከግለ-ሰቦች አልፎ ኅብረተሰቡን በማሸበር ላይ ያነጣጠረ የመዓት ውርጅብኝ በአገራችን ላይ እየወረደ ነው፡፡

ሕዝብን በውዴታ ማስተዳደር የማይችል ማንም ኃይል በጉልበትና በግድ አንበርክኮ ለመግዛት መሞከሩ የማይቀር እንደሆነ በታሪካችን ደጋግመን አይተነዋል፡፡ ይኸ ዓይነቱ አገዛዝ የሚቻለው ግን አንድ ሕዝብ ለአፋኞች ተንበርክኮ የጭቆናን ቀንበር ለመሸከም እስከቻለ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ሕዝብ ያለ ውዴታየ በግድ አልገዛም አሻፈረኝ ብሎ ሲነሳ ግን "ተራው" ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ብርክና ቀቢፀ-ተስፋነት አጥብቀው የሚጠናወቱት ኃይል ስለሚሆን ይኸንን ሕዝባዊ የአሻፈረኝ ተጋድሎ መጠን በሳተ ጭካኔ የተሞላበት ኃይል ለመደምሰስ ይሞክራል፡፡ በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ ተገዥዎች እንዲህ ዓይነቱ ታሪካዊ የፍጥጫ ደረጃ ላይ ከደረሱ ከገዥዎች ምንም ነገር መጠበቅ አይችሉም፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ታሪካዊ ትንንቅ በኅብረተሱ ላይ የሚወርደው ሽብር ከሽንፈትም በፊት በሚወርዱበት አመፅ የሚወሰን አይደለም፡፡ ሽንፈት ከመጣ ከዚህ ሽንፈት ባሻገርም ገዥዎችን ብርክ አስይዞ

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁ./Tel.:251-1574719;ፋክስ/Fax:2511574720

ሰሜን አሜሪካ (North America)
ፖ.ሣ.ቁ/P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ ቁ./Tel.: 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

የነበረው ተጋድሎ ተመልሶ እንዳያንሰራራ ቅስሙ በተሰበረ ኅብረተሰብም ላይ ጭካኔውና ሽብሩ እጥፍ ድርብ ሆኖ ተፋፍሞ ሰቆቃው ይቀጥላል። እሩቅ ሳንሄድ ተማሪ÷ አስተማሪ÷ ሰራተኛ አሰሪ÷ ወጣት ሽማግሌ÷ ወንድ ሴት÷ ገበሬ ከተሜና ምሁር ሳይል አንድ ታጋይ ትውልድን መሬት እንዲጠጣው ያደረገው እስከዛሬ ሰቆቃው ያለቀቀን የቀይ ሽብር ጠባሳ የየካቲት የዴሞክራሲ÷ የፍትኅና የብሔራዊ ነፃነት ህልም÷ ተስፋና ተጋድሎ በጥቂት የሥልጣን ጥመኞች አመፅ በተሸነፈ ማግስት በሕዝባችን ላይ የወረደ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሽንፈት መቋጠሪያ መዓት ነበር። ከታሪክ ተምረን ለዴሞክራሲና ለፍትኅ የምናደርገውም ተጋድሎ ተሸንፎ ግንቦትም የየካቲት እጣ እንዳይደርሰው መፍትሔ ከመፈለግና ተገቢውን መልስ ከማስገኘት ሌላ አማራጭ የለንም። ሕዝባችን በአንድ ትውልድ ዕድሜ እንዲህ ዓይነቱን መዓት ሁለቴ ለመሸከም የሚችል ትከሻ ስለሌለው ትግሉ ተፋፍሞ እስከ ድል መቀጠል ይኖርበታል። ሕዝባችን ከዚህና ትግሉ ከተሸነፈ ከሚጠብቀው የባሰ መከራና መዓት እራሱን ለመመከት ከራሱ ተጋድሎና መስዋዕትነት ሌላ ምንም መተማመኛ የለውም። አይኖረውምም። ይኽንን ተገንዝቦ በራሱ÷ በቆራጥነቱና በአንድነቱ ብቻ ተማምኖ ከእንግዲህ ለዴሞክራሲ መስፈን ብቻ ሳይሆን አገሩ እንደ አገር÷ ሕዝቡ እራሱ እንደ ሰብዓዊ ፍጡር ኅልውናቸው ጥያቄ ውስጥ ገብተዋልና የተያዘውን የአልሞት ባይ ተጋዳይ ትንንቁን አፋፍሞ መቀጠል ይኖርበታል። አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ከሕዝባዊ ድል በመለስ ሌላ አማራጭ ሊኖረን ስለማይገባ በዚህ ፍልሚያ መቀጠላችን የግድ ነው፤ እንቀጥላለንም።

በዚህ ታሪካዊ ወቅት ከዚህ አደጋ አንፃር የድርጅት÷ የብሔር÷ የሐይማኖት÷ ወዘተ... ስሌቶች ምንም ቦታ የላቸውም። አይኖራቸውምም። ታጋይ ኃይሎች በአገር ውስጥና በውጭ÷ በይፋና በህቡዕ÷ ሕጋዊ እውቅና ያላቸው ወይም የሌላቸው እየተባለ የሚከፋፈሉበት የቅንጦት ፈሊጥ ምንም ትርጉም የለውም። የወያኔ/ኢሕአዴግ አንድ የኅልውና ተስፋ ድርጅቶችንና ታጋይ ኃይሎችን በዚህ መልክ ከፋፍሎ እየፈረጀና ቅደም ተከተል እያወጣ ተራ በተራ መምታት÷ ሕዝብን በብሔር/ ብሔረሰብ÷ በአካባቢና በሐይማኖት ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎችን በአንድ በኩል "ዴሞክራሲያዊና ሕጋዊ" በሌላ በኩል ደግሞ በአክራሪና በአመፀኛነት ከፋፍሎ ሁሉንም ተራ በተራ ለማንበርከክ የመሞከር ስትራቴጅ እንደሆነ ግልጽ ነው። የዚያኑ ያኽል ደግሞ ለማንም ግልጽ መሆን የሚኖርበት ሌላ ቁም ነገር አለ። የሕዝቡ ትግል ድልን ሲጎናጸፍ ከዚህ የማይቋደስ ማንም ብሔር/ብሔረሰብ÷ ሐይማኖት÷ ድርጅት÷ ወዘተ... አይኖርም። ድሉ የሁላችንም ይሆናል። ሽንፈት ከመጣ ደግሞ ማንም ከመጭው መዓት አይተርፍም። ዛሬ የሕዝቡን ትግል ለማስተባበር ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወተው ወጣት÷ ሰራተኛ÷ ገበሬ÷ ምሁር÷ አገር-ወዳድና ዴሞክራት በወያኔ ሴራ ከተመታ ሌላም ከወዲሁ ግልጽ መሆን ያለበት ቁም ነገር አለ። የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች በጠራራ ፀሐይ ዘረፉ የሕዝብን ድል ሲቀሙ እየታየ "ሽንፈትን በፀጋ ለመቀበል" ስላልቻሉ ይኽንን የምርጫ ዙር እለፉና ለቀጣዩ በተሻለ ተደራጁ÷ ተዘጋጁ እያሉ የሚመክሩ ባዕዳን ይኽንን "ምክር" ተቀብለው ግንቦት 2002 ዓ/ም እንገናኝ እያሉ የሚዝቱ ተቃዋሚዎች በመኻላችን እንዳሉ ግልጽ ነው። እነዚህ ወገኖች መረዳት የሚኖርባቸው በአንድ በኩል ወያኔ/ኢሕአዴግ አሁን በሚያደርገው "ሥልጣን የሙጥኝ" አቋሙ ምክንያት የሕዝብን ድምፅ አፍኖ በኃይል ብቻ ለመግዛት በሚያደርገው አጉል ሙከራ ብዙ ወንጀል ውስጥ ስለሚነከር በአሁኑ ደረጃ ካለው የበለጠ በከረረና በጠነከረ አቋም በሥልጣን መቆየትን ብቻ የኅልውናው ዋስትና አድርጎ ስለሚያይ እንዲሁም እንደዛሬው የዛሬ አምስት ዓመትም የታጠቀና የመንግሥት ኃይል የሚቆጣጠር በመሆኑና በሌላ በኩል ደግሞ በዛሬው ሽንፈት ብቻ ሳይሆን በዚህ ቀጣይ የሽብር አዋጅ ሳቢያም ቅስሙ በተሰበረ ኅብረተሰብ ውስጥ ስለምንሆን ያኔ ፍዳችንን አይተንና ተሰውተን ድል አድርገን የተለመደው ሽፍጥ ከመጣ በትግል ድላችንን እናስከብራለን የምንልበት ምንም ዓይነት ተጨባጭ ምክንያት ስለማይኖረን ዛሬ መሸነፍ የኢትዮጵያችንን የአርነት ቀንና ብሩኅ ተስፋ ላልተወሰነ ረጅም ዘመን እንደማስተላለፍ ያህል ታሪካዊ ስህተት እየፈጸምን እንደሆነ ሁላችንም በተገቢና በምር መገንዘብ ይኖርብናል። ይቀጥላል....

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ! ኅዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም